የተከበራችሁ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ አዛዦች፣

የመንግሥት ኃላፊዎች እና ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣

እንዲሁም የተሰጣችሁን ሥልጠና አጠናቃችሁ ዛሬ ለተመረቃችሁ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት፤

ከሁሉ አስቀድሜ የሀገራችንን ሰላም፣ አንድነት እና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ የሚገባውን ውድ መስዕዋትነት ለመክፈል ፈቃደኛ በሆናችሁ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቼ እና እህቶቼ ፊት ቆሜ ንግግር እንዳደርግ ስለተፈቀደልኝ የተሰማኝን የላቀ ክብር እና ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ!

ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሀገረ መንግሥት ባለፈችባቸው በሺህ የሚቆጠሩ ዘመናት ከውስጥም ከውጪም ህልውናዋን እና የህዝቧን ሉዓላዊነት የሚፈታተኑ ችግሮች ቢገጥሟትም ለዘመናት ባዳበረችው ችግሮችን ተቋቁሞ የማለፍ ጥንካሬዋ የገጠሟትን ፈተናዎች ሁሉ በድል እየተሻገረች ካለንበት ዘመን ደርሳለች፤ በዚህ ዘመንም ሀገራችን ኢትዮጵያ የገጠማት ፈተና ከዚህ የተለየ አይደለም።

ሕወሃት እንደ ፖለቲካ ኃይል በኢትዮጵያ ምድር ከበቀለበት ጊዜ ጀምሮ ለሀገራችን ሰላም ለሕዝባችን እረፍት እንዳልነበረ ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። በተለይም ይኅው ኃይል የሀገሪቱን ማዕከላዊ የፖለቲካ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ዓ.ም በኋላ የፖለቲካ ስሪታችንን ብቻ ሳይሆን መልክዓ ምድሩን ጭምር በቋንቋ እና በማንነት ላይ ተመስርቶ እንዲሸነሸን በማድረጉ ዜጎች በሀገራችን ሉዓላዊ ግዛት ያለስቀቀን ተንቀሳቅሶ የመሥራት እና በመረጡት

ቦታ ሀብት አፍርቶ ቤተሰብ መሰርቶ የመኖር የዜግነት መብት አደጋ ላይ እንዲወድቅ አድርጓል። ይህ ሳያንሰው ለ27 ዓመታት የዘለቀው የህወሓት ግፈኛ አመራር በኢትዮጵያውያን ዜጎች የተባበረ እንቅስቃሴ ከማዕከላዊው ስልጣን ከተባረረ በኋላ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በሆደ ሰፊነት የተዘረጋለትን የይቅርታ እጅ ረግጦ የሀገራችን ሉዓላዊነት መገለጫ ምልክት እና የአንድነታችን ዘብ የሆነውን የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሰሜን ዕዝ ላይ አሰቃቂ ጥቃት በማድረስ የወንጀሎች ሁሉ ክፉ የሆነውን የሀገር ክህደት ወንጀል መፈፀሙ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ብቻ ሳይሆን በሀገራችን ታሪክም በቀላሉ የማይሽር ጠባሳ ትቶ ያለፈ ተግባር ነበር። ይህንን የሕወሃት እብሪት እና ሀገርን የማፍረስ ቅዠት የቀለበሰው የሉዓላዊነታችን ዘብ የሆነው ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን እና ሕወሃት ጥቃት ባደረሰባቸው ቦታዎች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ነው።

ሕወሃት በሰሜን ዕዝ ላይ ለፈፀመው አሰቃቂ የሀገር ክህደት ወንጀል ወዲያው ምላሽ የተሰጠው ቢሆንም አሁንም ድረስ የሀገር ሰላም፣ አንድነት እና ሉዓላዊነት አደጋ ዋነኛ ምንጭ መሆኑን ቀጥሏል። ይህ የጥፋት ኃይል የደቀነብን አደጋ የሀገራችን አንደነት፣ ሰላም እና ሉዓላዊነት ተጠብቆ ሁሉም ኢትዮጵያዊያንን በእኩልነት የሚያይ እና ዕኩል ዕድል የሚሰጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በተባበረ ክንድ ለመገንባት እንዲሁም ከድህነት ተርታ ለመውጣት ለምናደርገው ጥረት ዕንቅፋት ሆኗል።

አሁን የተደቀነብን አደጋ ኢትዮጵያዊያን ላይ በሙሉ የተደቀነ አደጋ በመሆኑ አደጋውን ለመመከትም ተባብረን በጋራ ልንቆም ይገባናል። አደጋውን ለመቀልበስ እና የሀገራችንን ሰላም እና አንድነት በማያዳግም ሁኔታ ለማረጋገጥ ኢትዮጵያዊያንን በሙሉ ያለምንም ልዩነት በጋራ አሰባሰቦ ሊያቆም የሚችለው እና ይህንንም ለማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው የሀገር መከላከያ

ሠራዊት እንደሆነ በፅኑ እናምናለን።

የሀገር መከላከያ ሠራዊታችን ጥብቅናው ለየትኛውም የፖለቲካ ኃይል ወይንም ዘውጌ ብሄረሰብ ሳይሆን ለሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እና ለዜጎች ሁሉ ሰላም በመሆኑ ዛሬ ሥልጠና የጨረሳችሁ የሠራዊቱ አባላት በዚህ ታሪካዊ መታጠፊያ ወቅት የተጣለባችሁን ኃላፊነት በከፍተኛ ወታደራዊ ብቃት፣ ቁርጠኝነት፣ ሀገር እና ወገን ወዳድነት እንዲሁም በኢትዮጵያዊ ጨዋነት እንደምትወጡ ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ።

ዛሬ ሥልጠናችሁን የጨረሳችሁትም ሆነ በሁሉ የሀገራችን አካባቢዎች የምትገኙ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት ለህይወታችሁ ሳትሳሱ ሀገር ተደፈረች ብላችሁ ሕይወታችሁን፣ ቤተሰባችሁን፣ ትምህረታችሁን፣ ትዳራችሁን፣ ቀያችሁን ትታችሁ፥ ከሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ተሰባሰባችሁ የጋራ ጠላታችንን በጋራ ለመመመከት ለምትሠሩት ሥራ ክብር አለን። ጦርነት ቀላል አይደለም፤ ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። ክቡር የሆነውን የሰው ሕይወት ይቀጥፋል፣ ያፈናቅላል፣ ያስርባል፣ ንብረት ያወድማል፣ ይከፋፍላል! ሁሉም ሰው ጦርነትን ሊፀየፍ እና እንዳይፈጠር ሊሠራ ይገባዋል። ነገር ግን በዘላቂነት ሕዝብ ላይ ተጣብቆ ዕለት ከዕለት መስዕዋትነትን የሚያስከፍለን አደጋ እንዳይመለስ አድርጎ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መቅበር ደግሞ የበለጠ አስፈላጊ ነው።

ማንኛውም ዓይነት ችግሮቻችን በንግግር እና በሰላማዊ ድርድር ተፈተው ሕዝብም ሠራዊታችንም መስዕዋትንት የማይከፍሉበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቢሆን መልካም ነበር። ያንን ዕድል ሠራዊታችን ላይ በተፈፀመ ጥቃት እንዳናገኝ ሆነናል። ፖለቲከኞች ተነጋግረው ሊፈቱት ይገባ የነበረ ችግር ተንከባሎ የንጹሀን ሕዝባችንን፣ ሠራዊታችን እንዲሁም በተለያያ ዘርፍ የተሰማሩ

የፀጥታ ኃይል አባላትን ሕይወት ወደማስገበር አድጓል። ኢትዮጵያ ዳግም ልጆቿ በተኙበት የማይታረዱባት፣ ንጹሀን ለፖለቲካ ፍጆታ የማይጨፈጨፉባት፣ እንድትሆን የሁላችንንም ቆራጥነት፣ መስዋዕትነት እና ሥራን ትፈልጋለች።

ሀገር የትውልድ ቅብብሎሽ ናትና በመስዋዕትነት ወደኛ የደረሰች ሀገር አሁንም የልጆቿን ያዳኝነት እጅ እያየች ትገኛለች። ሀገራችን የገጠማት ችግር ዘርፈ ብዙ ነው። አሁን ካለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ወደተሻለ ደረጃ መሸጋገር የምንችለውም ሁላችንም በየተሰማራንበት በታላቅ ወኔ እና ኃላፊነት ስንሠራ ነው። አንዳንዶቻችን ማስተማር፣ ሌሎቻችን መገንባት፣ ገሚሶቻችንን ደግሞ የፖለቲካ አማራጭ ማቅረብ ያሉብን ኃላፊነቶች ሲሆኑ የናንተ በተለየ ሁኔታ ሀገርን እና ሕዝብን ለማዳን እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የሚያስከፍል ኃላፊነትን ወስዳችኋል። እናንተ መስዋዕትነት ከፍላችሁ በምታመጡት ሰላም እና አንድነት ነው ሁሉም ሥራውን እና ኑሮውን መምራት የሚችለው። ስለዚህም ደማችሁን አፍሰሳችሁና አጥንታችሁን ከስክሳችሁ የምታቆይዋትን ሀገር አንድነቷ፣ ሉዋላዊነቷ እና ሰላሟ በዘላቂነት የተረጋረጠ አድርጎ ማቆየት የሁላችንም ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን እንደ ሀገር ቆመን የምትዋደቁለትን ዓላማ ለማሳካት እንደምንሠራ ቃል እንገባለን! እናንተ በአንድነት እንደቆማችሁ እኛም በአንድነት ቆመን ሀገርን እንጠብቃለን። ብሎም ከተጋረጠብን አደጋ ስንላቀቅ ለሀገራችን በችግሯ ጊዜ መድረሳችሁን እንረሳ ዘንድ ንፉጎች አይደለንም። በተዋደቀላት ሀገር ሠራዊታችን ተገቢውን ክብር አግኝቶ እንዲኖር በሙሉ አቅማችን እንሠራለን።

የሀገራችንን ሰላም፣ አንድነት እና ሉዓላዊነት በማያዳግም ሁኔታ ለማረጋገጥ፥ የመከላከያ ሠራዊታችን ተልዕኮውን እና ዘመኑን በሚመጥን ደረጃ ማደራጀት የቅድሚያ ቅድሚያ

የሚሰጠው ሀገራዊ ተግባር እንደሆነ እናምናለን። ኢትዮጵያውያን ዜጎችም ሠራዊታችንን በአባልነት በመቀላቀልም ሆነ የማይነጥፍ ድጋፍ በማድረግ ከጎናችሁ ለመሰለፍ ለአፍታም ቢሆን እንደማናመነታ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

በድጋሚ

ወድቃችሁ ስለምታቆሙን፤

ሞታችሁ ስለምታኖሩን፤

ስግብግብነት እና ሌብነት በነገሱበት ዘመን እራሳችሁን አሳልፋችሁ ስለምትሰጡን፤

ሆዳሞች ከድሀ ሲቆርሱ በበረሀ በርሀብ እና ጥም የሁላችን ደጀን ስለምትሆኑ፤

«እኔ ካልበላሁት ጭሬ ልበትነው» ባዩ በበዛበት፤ ሀገሬ ካንቺ በፊት እኛን ያስቀድመን ስላላችሁ፤

በጎጥ እና በመንደር ከፋፍለው ሊያባሉን ሲተጉ በኢትዮጵያዊነት ተሰባስባችሁ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር አንዲት እናታችሁን ስለምትጠብቁ፤

ሀገራችንን እና ሕዝባችንን ከነፍሳችሁ አስበልጣችሁ ስለወደዳችሁ፤

እናመሰግናችኋለን፤ እናከብራችኋለን!